የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

# <u>ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

**ሐምሌ 7 ቀን 2013 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ** - የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ለአዲሱ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፈቃድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ፈቃድ ሰጠ፡፡

በጨረታው ደንብ አንቀፅ 40 እና 41 በተደነገገው መሠረት የተመረጠው ባለፈቃድ (ዓለም አቀፍ አጋርነት ለኢትዮጵያ) ከተመረጠበት ቀን ጀምሮ በአርባ-አምስት (45) ቀናት ውስጥ የሀገር ውስጥ ኩባንያውን ማቋቋም እና የሀገር ውስጥ ኩባንያውም የንግድ ምዝገባውን ካጠናቀቀበት ዕለት አንስቶ በሶስት (3) የሥራ ቀናት ውስጥ በእናት ኩባንያው የተፈረመውን ጊዜያዊ የፈቃድ ስምምነት በስሙ በማዞር ዘላቂ የፈቃድ ስምምነት መፈረም ይጠበቅበታል፡፡

በዚህ መሠረት የተመረጠው ባለፈቃድ እና እናት ኩባንያ የሆነው ዓለም አቀፍ አጋርነት ለኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ኩባንያውን **ሳፋሪኮም ቴሌኮሚዩኒኬሽንስ ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር** ያቋቋመ እና የንግድ ምዝገባውን ያጠናቀቀ ሲሆን የሀገር ውስጥ ኩባንያውም የመጨረሻውን የፈቃድ ስምምነት በወቅቱ የፈረመ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ለሳፋሪኮም ቴሌኮሚዩኒኬሽንስ ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሐምሌ 2 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ለአስራ አምስት (15) ዓመት ፀንቶ የሚቆይ እና የፈቃድ ግዴታዎች ተሟልተው ከተገኙ ለተጨማሪ አስራ አምስት (15) ዓመት እየታደሰ የሚቀጥል በሀገር አቀፍ ደረጃ ሙሉ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችል የተቀናጀ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ሰጥቷል፡፡

መጨረሻ